








የሰው ሃዘን ጅማሬ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ 3-6

"የቃልህ ፍቺ ያበራል."
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ጸሐፊው Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው Byron Unger; Lazarus

የተተረጎመው Zemendale Translation Service
ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው) M. Maillot; Tammy S.

ታሪክ 2 ከ 60ዎቹ መሃከል

**M1914.org**

**Bible for Children, PO Box 3, Winnipeg MB R3C 2G1 Canada**

ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣
ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን
ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ
ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ
አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ
በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ
ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ
አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር
በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር
ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ
እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16

አማርኛ Amharic







"ከየትኛውም ዛፍ ፍሬ እንዳትበሉ እግዚአብሔር ተናግሯችሁ ነበር? በማለት እባቡም ሔዋንን ጠየቃት።" ከሁሉም ዛፎች ፍሬ እንድንበላ ፍቅዶልናል ነገር ግን አንዲት ፍሬዋ የማይበላ ዛፍ እንዳለች ነግሮኛል። "እባቡም አትሞቱም" ብሎ መለሠላት።
3
"እንደ እግዚአብሔርም ትሆናላችሁ" አላቸው። ሔዋንም ከዚያ ዛፍ ፍሬን ለመብላት አሠበች እባቡንም ሠማች እንዳላት ብዚያች ዛፍ ፍሬን በላች።
4
ሔዋንም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ከተላለፈች በኋላ ባሏም አዳም ከዚያች ዛፍ ፍሬን እንዲበላ ሰጠችው እሱም በላ። አዳምም ስትሰጠው "አይሆንም የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ልንተላለፈው አይገባም" ማለት ነበረበት።
5
አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ከሠራ ወይም ካደረጉ በኋለ እርቃናቸውን መሆናቸውን አወቁ። ለሀፍረታቸው መሸፈኛ ይሆን ዘንድ ቅጠል ሰፈተው ሀፍረታቸውን ሸፈኑት ከቁጥቋጠው ሥር በመሸሽግም ከእግዚአብሔር ተደበቁ::
6
ፀሐይም ባዘቀዘቀች ጊዜ እግዚአብሔርም ወደ ኤደን ገነት ውስጥ መጣ። አዳምና ሔዋን ያደረጉትን ያውቅነበርና። አዳምም በሔዋን ላይ አመካኘ ሔዋንም በእባብ አመካኘች። እግዚአብሔርም እባብን "የተረገምክሁን። ሴትቱም በወላጀዋ ጊዜ በምጥ ትውለድ" ብሎ ረገማቸው። "አዳም አንተ ኃጢአትን ከመሥራትህ የተነሣ ምድር ተረገመች እሾህንና አሜክላን ታብቅል። ጥረህ ግረህ የላብህን ወዝ ፈሬዋንም ብላ" አለው።
7
እግዚአብሔርም አዳምና በሔዋንን ከኤደን ገነት ውስጥ አሰወጣቸው ምክንያቱም ኃጢአትን ሠርተዋልና ህይወት ሰጪ ከሆነው እግዚአብሔር ተለይተዋል።
8
እንደ እሳት የሚንበለበሉ ሰይፎችንም እግዚአብሔር በኤደን ገነት ውስጥ አኖረ አስወጣቸውም እግዚአብሔርም ለአዳምና ለሔዋን የበግ ለምድን አለበሳቸው።
9
እግዚአብሔር ይህንን እግዚአብሔርም ለአዳምና ለሔዋን የበግ ለምድን አለበሳቸው። እግዚአብሔርም ይህንን ለምድ ከየት አመጣው?
10
በጊዜው አዳምና ሔዋን ልጆችን ወለዱ። የመጀመሪያ ልጃቸውም ቃየል አትክልተኛ ነበር። ሁለተኛው ልጃቸውም አቤል ይባላል እሱም እረኛ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ቃየል ለአምላኩ ለእግዚአብሔር ከእርሻው ሰብል ስጦታን አመጣለት። አቤልም በጣም ምርጥ ከሚላቸው በጎች መሃከል አንዱን መርጦ ለእግዚአብሔር በስጦታ መልክ አመጣለት። እግዚአብሔርም በአቤል ስጦታ በጣም ደስ ብሎት ነበር።
11
እግዚአብሔር በቃየልና በመሥዋዕቱ ደስተኛ አልነበረም። ቃየልም በጣም ተናደደ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲህ አለ "ትክክለኛውን ነገር ካደረግክ ተቀባይነትን አታገኝምን?"
12
የቃየልም ንዴት ከውስጡ አልጣፋም ነበር። ከእርሻው በኋላ ወንድሙን አቤልን አደጋ አደረሰበት ከዚያም በኋላ ገደለው።
13
እግዚአብሔርም ቃየልን እንዲህ አለው "ወንድምህ አቤል ወዴት አለ?" "ከወዴት እንዳለ አላውቅም" ብሎ ዋሸው። "እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን?" አለው። እግዚአብሔርም አቤል በመዋሸቱና እራሱን አዳኝ በማስመሰል አራሽ (ገበሬ) ሆኖ ሥጦታን በውሸት በማቅረቡ ነው።
14
ቃየልም ከእግዚአብር ፊት ሸሽቶ ሄደ። እሱም የአዳምንና የሔዋንን ልጅ አገባ፡ ቤተሰባቸውንም አሣደጉ። በቅርቡም የቃል የልጅ ልጆችና፣ የልጅ ልጅ ልጆች ቃየልም የመሠረታትን ከተማ ሞሉትት፡
15
የአዳምና የሔዋን ቤተሰብ በፍጥነት አደገ። በዚያን ዘመን የነበሩ ሠዎች ዛሬ ከሚኖሩት ሠዎች ይልቅ ረጅም ዕድሜ አላቸው።
16
ሴት ልጇ ሴት በተወለደችበት ጊዜ ሔዋን እንደህ አለች "በአቤል ምትክ እግዚአብሔርን ሴትን ሰጥቶኛል ሴትም ብዙ ልጆችን ወለደ 912 ዓመት ኖረ።
17
በዚህ ዓለም ውስጥ በተለያዩ ትውልዶች መሃከል ዓመጽ እየበዛ መጣ፤ በመጨረሻም እግዚአብሔር የሠውን ልጆች ለማጥፋት ወሠነ። ሁሉም አውሬዎችና እንስሳት። እግዚአብሔር ሰው በመፍጠሩ ተጸጸተ። ነገር ግን አንድ ሰው እግዚአብሔርን አስደሰተ።
18